የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፵፭
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፳፪ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No. 45
ADDIS ABABA,30th April , 2015

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፺/፪ሺ፯ ዓ.ም
የኪዮቶ ፕሮቶኮል ማሻሻያ ማፅደቂያ አዋጅ............................................................ገጽ ፰ሺ፪፻፵፭

CONTENTS

Proclamation No. 890/2015
Kyoto Protocol Amendment Ratification Proclamation ............................................................page 8245

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፺/፪ሺ፯

## የግሪን ሀውስ ጋዝ ልቀት መጠን መቀነስን በሚመለከት የኪዮቶ ፕሮቶኮል ማሻሻያን ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ የማዕቀፌ ስምምነትን ተግባራዊ ለማድረግ ህዳር ፳፱ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም የወጣው የኪዮቶ ፕሮቶኮል የተሻሻለ ስለሆነ፤

ይህንኑ የተሻሻለውን የኪዮቶ ፕሮቶኮል የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፳፪ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION No.890 /2015

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE RATIFICATION OF THE AMENDMENT TO THE KYOTO PROTOCOL ON THE REDUCTION OF GREEN HOUSE GASES

WHERE AS, the Kyoto Protocol adopted on the 8th of December 2012 to implement the United Nations framework Convention on climate Change has been amended;

WHERE AS, the House of the Peoples' Representatives of the Federal democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Protocol at its session held on the 31st day of the March 2015;

NOW THEREFORE; in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia ,it is here by proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 5.10

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የኪዮቶ ፕሮቶኮል ማሻሻያ ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፺/፪ሺ፯"ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪.<u>የፕሮቶኮል ማሻሻያው መፅደቅ</u>**

የግሪን ሀውስ ጋዝ ልቀት መጠን መቀነስን በሚመለከት ህዳር ፳፱ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም የወጣው የኪዮቶ ፕሮቶኮል ማሻሻያ ስምምነት ፀድቋል፡፡

**፫.<u>የአካባቢና የደን ሚኒስቴር ስልጣን</u>**

የአካባቢና የደን ሚኒስቴር ሀላፊነት ካላቸው የፌደራል፣ የክልል፣ የከተማ መስተዳድርና የመንግስት መስሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር የኪዮቶ ፕሮቶኮል ማሻሻያ ስምምነትን በስራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሃላፊነት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል ፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሚያዚያ ፳፪ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This proclamation may be cited as the " Kyoto Protocol Amendment Ratification Proclamation No.890/2015."

**2. <u>Ratification of the Protocol</u>**

The Amendment to the Kyoto protocol on the Reduction of Greenhouse Gases, adopted on the 8th day of December 2012, is hereby ratified.

**3. <u>Responsibility of the Ministry of Environment and Forest</u>**

The Ministry of Environment and Forest is hereby authorized to take, in cooperation with the appropriate Federal, Regional, and City Administration Government ,actions necessary to implement the Amendment protocol.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 30th day of April, 2015.

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት